# ተንኮለኛ ድንጋይ

ተንኮለኛ ድንጋይ ፣ከሆዴ ውስጥ ገብታ፣
ምንም ሳልጠረጥር ፣ ቀስ ባላ አዘናግታ፣
የሃሞት ከረጢቴን ፣ቱቦውንም ዘግታ፣
ልትገለኝ ነበረ ፣ በጣም አንገላታ።

ከስንቱ መርዛ መርዝ፣ አሸዋ ከባሰ ፣
መከራ ካበዛ ፣ ሰው ካላላወሰ
እሆድ ውስጥ ገብቶ፣ ካላንቀሳቀሰ፣
አሸዋ አሸንፎ ፣ ሰው ላይ ከነገሰ፣
የሰው ሰውነቱ ፣ አበቃ ጨረሰ፣

ለምትወዱት ሁሉ ፣አፈር ልብላ አትበሉ፣
ወደሆድ ከገባ ፣ ወርዶ በቀላሉ፣
አፈር አንፈራፍሮ፣ ተቀይሮ አመሉ፤
ድራሹን ያጠፋል ፣ውስጥ አንጀትን ሁሉ
ሁለተኛ ባፈር ፣ በስሙ እንዳትምሉ፣
ከሞት መች ያንስና፣ ካምሳያ መሰሉ ።

በልጅግ

ጀርመን የካቲት 2010